# ለጠቢያም የሚታዘንለት መሪ ጣልላት!

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

እንደኔ እንደኔ ማየት መልካም አንዳንዴ ግን ጎጂም ነው። ሰሞኑን የተከበሩ ኢድዋርድ ኬነዲ ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን ተከትሎ መልካም ነገር አይቻለሁ። በጎ የሰራ ሲሞት ወፍ አሞራው ሲያለቅስ ማየት ለኔ የመጀመሪያዬ ጊዜ አይደለም። እንደምታውቁት በአገራችን በጎ ነገር በህይወቱ የሰራ ይህችን ሰው እንደ አውሬ የሚናከስባትን አለም ትቶ ሲሄድ የሰፈርና የአገር ሕዝብ ፊቱን እየነጨ ሐዘኑን ይገልጻል። አዲስ አመት፣ መስቀል፣ ገና፣ ፋሲካ፣ የፍልሰታ ግድፍት በመጣ ቁጥር አቅም የሌላቸውን ጎረቢቶቻችንን ልጆች ሳትመግብ ለእኛ ለልጆቿ ምግብ የማታቀርበው እናቴ ስታርፍም ወፊ አሞራው በእንባ ተራጭቷል። ነገር ግን በአመራር ቦታ ላይ ያለ ሰው ሲሞት በመላ አገሪቱ በዚህ ደረጃ ሲታዘንለት ማየት ለእኔ አዲስ ነገር ብቻ ሳይሆን ተአምርም ነው።

አብዛኛው አንባቢ ተገንዝቧል ብዬ እንደምገምተው ከሃምሳ ሺህ ሕዝብ በላይ እስከ አምስትና ስድስት ሰአት ሰልፍ ይዞ እየጠበቀ የእኒህን የተከበሩ ሰው አስከሬን ተሳለመ። ስንቱ አስከሬናቸው ለሚጓዝበት መኪና ሰገደ፣ ለሰጡት አገልግሎት አመሰገነ፤ ነፍሳቸው እንዲማርም ጸሎቱን አደረሰ፤ በማድረስ ላይም ነው። ይህ በጎ ስራቸው ለዘላለም ሲወሳም ይኖራል። አዎ ልብ ስፍስፍ፣ አንጀት ልውስ እስከሚል ድረስ የሚታዘንለት የህዝብ ተወካይ መገኘቱ ለእኔ እንግዳ ነገር ነው። ይህንን አስገራሚ ትይንት በማየት ላይ እንዳለሁ እንደ ወትሮው ሁሉ አእምሮዬ የሰው ዘር መገኛ ናት ወደሚባልላት ነገር ግን ዛሬ በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን እንኳን የሰው ልጅ በባሩድ፣ በርሃብና በተላላፊ በሽታ እንደቅጠል ወደሚረግፋት ወደኛው አገር ተሻገረና በመንፈስ እጅጉን ተጎዳሁ። በእድሜ አስርና አስራምስት እጅ እንበልጣቸዋለን የምንላቸው ሰዎች እኛ ሰው መርጦ ባልተወለደበት ቋንቋውና ዘሩ እንደከብት በመከለል ወደ ሁዋላ ስንሽመደመድና ስንንከባለል እነሱ በአለም ላይ ያለውን የሰው ዘር ሁሉ በሰውነቱ ብቻ አክበረው ይዘው በኤሌክትሮኒክስ ፍጥነት በሁሉም መስክ ጥለውን መጠቁ።

የልብን ሁኔታ በትክክል የሚያውቀው ሰው ያልሆነው አምላክ ነው። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን ሚስተር ኢድዋርድ ኬነዲን ልዩ የሚያደርጋቸው ሕዝብን በቀለም፣በዘር፣በሐብት መጠንና በሌሎችም አናሳ መስፈርቶች ሳይለዩ ማገልገላቸው ነው። አዎ በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በጎጥና ሌሎችም የጤነኛ ሰው አስተሳሰብ ባልሆኑ ጉዳዮች የሚያምንና ሕዝብን የሚከፋፍል ቆሞ ሳለ ይለቀስበታል ሲሞት ግን የደስታ ዘፈን ይዘፈንበታል። እርግጥ ነው እንዲህ አይንቱ ከንቱ ሰው በህይወት እያለ "የርሱን ነገር ሰማይን ካለምሰሶ ያቆመ አምላክ ያሳየኝ!" እያለ ልጅ አዋቂው እንባ ያፈስበታል ሲሞት ደግሞ "የብጹአን አምላክ ደግ ነገር አደረክልን!" እያለ አምላክን ከቤተ-ክርስቲያን ወይም ከመስጊድ ፊት ለፊት ተንበርክኮ ያመሰግንበታል። ሰማይ ቤት ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም አንድ ሰው ቆሞ ሕዝብ በዚህ መልክ ካለቀሰበትና ሲሞት ደግሞ ከተደሰተበት ይህ ሰው እየኖረም ሆነ ሞቶ ኩነኔ ውስጥ ነው ባይ ነኝ።

ስንቶች ተስለው ወይም በጉልበታቸው ተንበርክከው ጸልየው ልመናቸው ሳይሞላላቸው ያለፉትን ጠቢያውያን እያስታወሳችሁ "ያንተ የከንቱው ልመና ምን ሊያመጣ!" ልትሉኝ ትችላላችሁ። በዚህ ይህችን ጦማር በምሞነጫጭርበት ሰዓት እኔ አምላክን የምለምነው ሐብት ጨምርልኝ፣ ወርዱን አጥብብልኝ ወይም አስፋልኝ ብዬ አይደለም። ለጠቢያም በአምሳልህ ተፈጥሮ ሁሉንም የሰው ልጆች በእኩል አይን የሚያይ፣ ወላጅን በመግደል ልጅን ካለአሳዳጊ የማያስቀር፣ ልጆችን እንደ ቅጠል በመጨፍጨፍ ወላጆችን በዘላለም ሐዘን ውስጥ የማይዘፍቅ፣ ዜጎችን በከንቱ የማያስር፣ የማያሰድድ፣ ሌተ ተቀን የማይቀጥፍ፣ የማይዘርፍ፤ ሕዝብን በርሃብና በበሽታ አለንጋ የማይገርፍ፤ ባጎሳቆለው ሕዝብ ስም እየለመነ የማይበላ፤ በአጠቃላይ የሚታዘንበት ሳይሆን የሚታዘንለት የሕዝብ ተወካይ ወይም መሪ ጣልላት ብዬ ነው። አመሰግናለሁ።

*ነሐሴ ፳፬ ቀን ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*